የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ
# ADDIS NEGARI GAZETA
OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሰላሳ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፸፮
አዲስ አበባ ሰኔ ፲ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ/ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32th Year No.76
Addis Ababa 17th day of Jun, 2024

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፻፹/፪ሺ፲፮
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ብክለት መከላከል ደንብ

ገፅ............................................ ፫ሺ፯፻፹፱

CONTENTS

REGULATION No. 180/2024
A REGULATION TO PROVIDE FOR RIVERBANK DEVELOPMENT AND POLLUTION PREVENTION THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

Page ………………….…………………… 3789

## ደንብ ቁጥር ፻፹/፪ሺ፲፮
## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ብክለት መከላከል ደንብ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና አንቀጽ ፺፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሁሉም ሰዎች ንጹሕና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት እንደአላቸውና መንግሥትም ንጹሕና ጤናማ አካባቢ እንዲኖራቸው የመጣር ኃላፊነት እንደአለበት የተደነገገ በመሆኑ፤

## REGULATION No. 180/2024
## A REGULATION TO PROVIDE FOR RIVERBANK DEVELOPMENT AND POLLUTION PREVENTION THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

**WHWREAS,** it is provide by all people have the right to live in a clean and healthy environment and that the government has the responsibility to strive to have a clean and healthy environment in accordance with Sub Article (1) of Article 44 and Sub Article (1) of Article 92 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፰) የከተማው አስተዳደር የአካባቢ ብክለትን በመከላከል ከተማውን የተፈጥሮ ሚዛኑን የጠበቀ፣ ጽዱ፣ አረንጓዴና ምቹ ማድረግ በዓላማ ደረጃ የተደነገገለት በመሆኑ በከተማው ውስጥ የሚገኙ ወንዞችና ዳርቻዎቻቸው ንጹሕና ጤናማ አካባቢ እንዲሆኑ ማድረግ በማስፈለጉ፤

በከተማው ውስጥ የሚገኙ ወንዞችና የወንዝ ዳርቻ እና ገባሮቻቸው ከተለያዩ የመኖሪያ ቤቶች፣ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዲሁም ፋብሪካዎች በሚወጣው በካይ ፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻዎች ምክንያት ተፈጥሯዊ ባህሪ ተቀይሮ ለሰዎች ጤናና ደህንነት ጎጂ በመሆናቸው፤

የከተማዋን ወንዝና ዳርቻውን ከብክለት በመጠበቅና በማስተዳደር፤ እንዲሁም የተፈጥሮ ይዘቱን እንዳይቀይር በማድረግ፤ የሰውን ጤንነት፤ ከማስጠበቅና ህይወት ያላቸውና የሌላቸውን በወንዝና በወንዝ አካባቢ የሚኖሩትን የተፈጥሮ ሥነ-ህይወታዊ አካላትን ማቆየትና ማስቀጠል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የወንዝ ብክለትን ለመከላከል የተቀመጡ አሰራሮች ተግባራት በማይፈጽሙ አካላት ላይ ተመጣጣኝ ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃ በመውሰድ ከጥታፋቸው ተምረው ከተመሳሳይ ድርጊት እንዲታቀቡና የደረሰውን ጉዳት በማስተካከል ወደነበረበት እንዲመልሱ ማድረግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት በሕግ መዘርጋት አስፈላጊነቱ ስለታመነበት፤

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፭ አንቀጽ ፺፬ መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

**WHWREAS,** it has become necessary to the city administration is required to prevent environmental pollution and make the city clean, green and comfortable, maintaining its natural balance, and thus making the rivers and their banks in the city a clean and healthy environment in accordance with Sub Article (8) of Article 9 of the revised Charter of Addis Ababa City Government Proclamation No. 361/1995;

**WHWREAS,** the rivers and riverbanks and their tributaries in the city have changed their natural behavior due to the polluting sewage and solid wastes coming out from various residences, service institutions, factories and are harmful to people's health and safety;

**WHWREAS,** it has been found necessary to preserve and maintain the living and non-living natural biological elements living in and around the river, keeping it from changing its natural content. Human health by protecting and managing the city's river and its shores from pollution;

**WHWREAS,** it is believed that setting up working procedure by taking appropriate legal and administrative action against those who do not carry out the activities of the procedures laid down to prevent river pollution. That will enable them to learn from their mistakes and refrain from similar actions and restore the damage caused by them;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 94 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Re-specify the Power and Duties of the thereof Proclamation No. 84/2023, the Cabinet of Addis Ababa City Government has issued this Regulation.

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩.አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ብክለት መከላከል ደንብ ቁጥር ፻፹/፪ሺ፲፯ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪ትርጓሜ**

የቃሉ ወይም የሐረጉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩ **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪ **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫ **"ቢሮ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ ነው፤

፬ **"ባለስልጣን"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ነው፤

፭ **"አካባቢ"** ማለት በመሬት በአካባቢ አየር፣ በአየር ሁኔታ እና በአየር ንብረት፣ በውሃ፣ በህያዋን፣ በድምጽ፣ በሽታ፣ በጣዕም፣ በማህበራዊ ጉዳዮች እና በስነ ውበት ሳይወሰን በተፈጥሯዊ ሁኔታዎች ወይም በሰው አማካኝነት ተሻሽለው ወይም ተለውጠው የሚገኙ ነገሮች በጠቅላላ ያሉበት ቦታ እንዲሁም መጠናቸው ወይም ሁኔታቸው የሰው ወይም የሌሎች ህያዋንን የሚነኩ መስተጋብሮች ድምር ነው፤

፮ **"ኬሚካል"** ማለት ኤለመንት ወይም ያልተቀላቀለ ቀለም ይሁን የተቀላቀለ ውህድ ወይም ተቀምሞ በሰው የተሰራ ወይም ከተፈጥሮ የተገኘ ቁስ አካል ነው፤

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as "Riverbank Development and Pollution Prevention the City Government of Addis Ababa Regulation No. 12/2024".

2. **Definition**

Unless the context or phrase requires otherwise in this regulation:

1. "**City**" means the Addis Ababa city;
2. "**Administration**" means the city government of Addis Ababa;
3. "**Bureau**" means the Urban Beautification and Green Development Bureau the city government of Addis Ababa;
4. "**Authority**" means the Environmental Protection Authority the city government of Addis Ababa;
5. "**Environment**" means the totality of all materials whether in their natural state or modified or changed by human; their external spaces and the interactions which affect their quality or quantity and the welfare of human or other living beings, include but not restricted to, land atmosphere, whether and climate, water, living things, sound, odor, taste, social factors, and aesthetics;
6. "**Chemical**" means an element or a compound whether by itself, or in a mixture or a preparation, whether manufactured or obtained from nature;

፯. **"ቆሻሻ"** ማለት ማናቸውም በጠጣር፣ በፈሳሽ ወይም በትነት (ጋዝ) መልክ ወደ ማናቸውም የወንዝ አካል የሚጨመር የሚለቀቅ ወይም የሚደፋ ጎጂ ነገር ነው፤

፰. **"አደገኛ ቆሻሻ"** ማለት ተፈላጊነት የሌለው ሆኖ በአካባቢ ወይም በሰው ደህንነት ወይም ጤና ላይ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ የሚታመን ማንኛውም ነገር እና በአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺/፪ሺ፲ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፤

፱. **"ውሃ"** ማለት የገፀ ምድርና የከርሰ ምድር ውሃ ነው፤

፲. **"መልቀቅ"** ማለት በውል ታስቦም ይሁን ሳይታሰብ በካይን ወደ ማንኛውም የአካባቢ ክፍል መጨመር ነው፤

፲፩. **"ወንዝ"** ማለት በከተማው መዋቅራዊ ፕላን መሠረት የተለዩ ከአንድ የተወሰነ ቦታ የሚመነጭና በትናንሽ ገባር ፈሳሾች ዳብሮ ረጅም ርቀት የሚጓዝ ወራጅ ወይም በመሬት ውስጥ በተፈጥሮ ቦይ የሚፈስ ጨዋማ ያልሆነ ውኃ ሲሆን ወደ ሌሎች አጎራባች ክልል ወይም ወደ ሌላ ወንዝ የሚፈስ ወይም ከወንዝ ጋር ተያያዥነት ያለው ሰው ሰራሽ ሀይቅ፣ ምንጭ እና ገባር ወንዝን ያካትታል፤

፲፪. **"የወንዝ ዳርቻ"** ማለት ለወንዝ ዳርቻ መጠበቂያ ቢያንስ ከወንዙ ጠርዝ ግራና ቀኝ ዝቅተኛው ፴ ሜትር ሆኖ እንደአካባቢው ሁኔታ አስተዳደሩ በሚወስነው መሠረት ስፋቱ ሊጨምር የሚችል ሲሆን ለማንኛውም ዓይነት ግንባታ ወይም አገልግሎት እንዲውል የማይፈቀድ ቦታ እና በወንዙ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ሥፍራ ነው፤

7. "**Waste**" means any harmful substance in solid, liquid or vapor (gas) form that is discharged or discharged into any body of a river;

8. "**Hazardous Waste**" means any unwanted material that is believed to be deleterious to human safety or health or the environment and shall have the meaning given by Hazardous Waste Management and Disposal Control Proclamation No. 1090/2010;

9. "**Water**" means surface and ground water;

10. "**Release**" means discharging of hazardous wastes to the environment intentionally or negligently;

11. "**River**" means non-saline water that originates from a certain place and travels long distances through small tributary streams or a natural channel in the ground that flows to other neighboring regions or another river or an artificial lake or spring that is connected to the river and includes a tributary;

12. "**Riverbank**" means the minimum 30 meters from the river bank to the right and left side of the river bank, the width of which can be increased according to the local conditions and the area that is not allowed to be used for any kind of construction or service and the area that affects the river;

፲፫ **“የወንዝ ብክለት”** ማለት የከተማዋ ወንዞች ከማንኛውም ግለሰብ፤ መኖሪያ ቤት፣ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በሚመነጩ የተለያዩ በካይ ነገሮች ምክንያት የወንዝን ተፈጥራዊ ባህሪ መቀየርን የሚያመለክት ነው፤

፲፬ **“የወንዝና ወንዝ ዳርቻ ኮሪደር ልማት”** ማለት ከወንዙ ተፋሰስ መነሻ ጀምሮ የሥነ-ምህዳር ጥበቃ፣ አረንጓዴ ልማት፣ መዝናኛ ቦታዎችን እና ተያያዥ አገልግሎቶችን ከወንዙ ኩታ ገጠም የሆኑ አካባቢዎች ማልማት ሆኖ ወሰኑና የመሬት አጠቃቀሙ በጥናት የሚወሰን ይሆናል፤

፲፭ **“ደረቅ ቆሻሻ”** ማለት ከማንኛውም መኖሪያ ቤት፣ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚመነጭ የማይፈለግ ተብሎ የተጣለ ፈሳሽ ወይም ፈሳሽ ያልሆነ ነገር ወይም ከቄራዎች አካባቢ የሚፈጠር የሞተ እንስሳ አካል፤ በድን፤ አጥንት፤ ጸጉር፤ ቆዳ ወይም ቅርፊት ነው፤

፲፮ **“ፍሳሽ ቆሻሻ”** ማለት ከመኖሪያ ቤት፣ ከኢንዱስትሪ፣ ከጋራዥ፣ ከማናኛውም መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የሚወጣ የልብስ ፣የምግብ እቃዎች፣ የመጠጥ እቃዎች እጣቢ፣ አተላ፣ አምቡላ፣ የመጸዳጃ ቤት ፍሳሽ፣ የእንስሳት ማደሪያ ፍሳሽና መርዛማ ንጥረ ነገር ያዘለ ወይም ያላዘለ ፍሳሽ የመሳሰሉት ነው፤

፲፯ **“በካይ”** ማለት ፈሳሽ፤ ጠጣር ወይም ጋዝ የሆነ በቀጥታም ሆነ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ፡-

ሀ) ያረፈበትን የወንዝ ክፍል ጥራት በመለወጥ ጠቃሚታ የመስጠት አቅሙን የሚያጓድል ወይም፣

13. "**River Pollution**" means the rivers of the city from any individual; It refers to the changing of the natural characteristics of a river due to various pollutants generated by housing, production and service facilities;

14. "**River and Riverbank Corridor Development**" means ecological protection from the source of the river basin; decided to develop green development, recreational areas and related services in the areas facing the river side by side and the land use will be determined by the study;

15. "**Dry Waste**" means any liquid or non-liquid matter or dead animal body from the area of slaughterhouses, which is discarded as unwanted from any housing, manufacturing and service establishments; dead bone hair It is skin or bark;

16. "**Sewage Waste**" means clothes, food items, drinking water laundries, slime, dregs, toilet sewage, animal shelter sewage and toxic or non-toxic substances coming out of homes, industries, garages, and any governmental and non-governmental organizations;

17. "**Pollutant**" means any substance whether liquid, solid, or gas which directly or indirectly:

a) alters the quality of any part of the receiving environment so as to effect its beneficial use adversely; or

ለ) በሰው ጤና ወይም በወንዝና በወንዝ ዳርቻ ውስጥ ያለውን ብዝሃ ህይወትና ሥርዓተ ምህዳር ላይ ጉዳት የሚያደርስ ወይም ሊያደርስ የሚችል መርዝ የሚያመነጭ ማንኛውም ነገር ነዉ፤

፲፰. **"የወንዝ ሥርዓተ-ምህዳር"** ማለት በወንዝና በወንዝ ዳርቻ ያሉ ማናቸውም ሕይወት ያላቸው ነገሮች ከራሳቸው ጋርም ሆነ ሕይወት ከሌላቸው ነገሮች እንዲሁም ከአካባቢያቸው ጋር የሚያደርጉትን ያልተቋረጠ ተፈጥሮአዊ መስተጋብር የሚያሳይ ሥርዓት ነው፤

፲፱. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፫. **የተፈጻሚነት ወሰን**

፩. ይህ ደንብ በአስተዳደሩ አስተዳደራዊ ወሰን ውስጥ በሚገኙ ወንዞችና የወንዝ ዳርቻዎች፤ እና

፪. በወንዝና በወንዝ ዳርቻ እና በአካባቢው ደህንነት ላይ ብክለትና አሉታዊ ተጽእኖዎችን በሚያስከትል ማንኛውም ሰው፣ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**ክፍል ሁለት**

**የወንዝና የወንዝ ዳርቻ ልማት፣ ከብክለት መከላከል እና መንከባከብ**

፬. **የወንዝና የወንዝ ዳርቻ ስለማልማት፤**

፩. የወንዝና የወንዝ ዳርቻ ለማልማት የሚያስችል መረጃ በመሰብሰብ፤ በማደራጀት እና በመተንተን የተለያዩ የልማት ሥራዎችን በመደበኛ የልማት ፕሮግራሞች ወይም በፕሮጀክት መልኩ ተግባራዊ ማድረግ፤

b) produces toxic substances, diseases, objectionable odour, radioactivity, noise, vibration, heat, or any other phenomenon that is hazardous to human health or to other living things;

18. "**River Ecosystem**" means a system that shows the continuous natural interaction of any living things in a river and along its banks with themselves or with non-living things and their environment;

19. "**Person**" means any natural or juridical person.

3. **Scope of Application**

1. This Regulation shall be Applicable to rivers and riverbanks within the administrative boundaries of the administration; And

Any person who causes pollution and adverse effects on the river, its banks and the safety of the environment

**PART TWO**

**RIVER AND RIVERBANK DEVELOPMENT, POLLUTION PREVENTION AND PROTECTION**

4. **Development of River and Riverbanks**

1. Collecting information to develop rivers and riverbanks; Organizing and analyzing various development activities in regular development programs or projects;

፪ የወንዝና የወንዝ ዳርቻ ልማት ሥራ ከመሰራቱ በፊት በወንዝ ዳርቻ ክልል ውስጥ ስለሚኖር ነዋሪ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥናቶችን ያካተተ ዝርዝር የአካባቢ ልማት እቅድ ማዘጋጀት፤

፫ የሚዘጋጅ ዝርዝር የአካባቢ ልማት ጥናት በቀጣይ የወንዝና የወንዝ ዳርቻ ልማት ተከትሎ የሚመጣውን የገጽታ ለውጥ ታሳቢ ያደረገ የወንዝ ኮሪደር ልማትን ያካተተ እንዲሆን ማድረግ፤

፬ ወንዝና የወንዝ ዳርቻ እንዲለማ ሲደረግ ከላይኛው የተፋሰስ ክፍል በመነሳት ያለማቋራረጥ ወደታችኛው የወንዝ ክፍል መሆኑን ማረጋገጥ፤

፭ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌ ቢኖርም በአስተዳደሩ ሲወሰን በማንኛውም የታችኛው የወንዙ ክፍል ላይ ልማት ማካሄድ፤

፮ አግባብነት ካለው የአስተዳደሩ ተቋም ጋር በመሆን የወንዝ ዳርቻ ወሰኖችን በመለየት ከሚመለከተው አካል የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማውጣት፤ ቦታዎቹን ማስተዳደር፤ መጠበቅ፤

፯ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የወጣለትን የወንዝና የወንዝ ዳርቻ ቦታና ሌሎች በኃላፊነት የሚያስተዳድራቸውን አረንጓዴ ቦታዎች የይዞታ ምዝገባ ማረጋገጫ ዲጂታል ካርታ ማውጣት፤

፰ በከተማ አስተዳደሩ መዋቅራዊ ፕላን፣ መዋቅራዊ ፕላኑን ለማስፈጸም በሚዘጋጁ ዝርዝር የአካባቢ ልማት ጥናቶች እና የሽንሻኖ ፕላኖች የሚለዩ የወንዝ ዳርቻ ቦታዎችና ሌሎች አረንጓዴ ቦታዎችን ከሚመለከታቸው አካላት መረጃ በመሰብሰብ ዝርዝር ዲዛይኖች ተዘጋጅቶላቸው እንዲለሙ ማድረግ፤

2. Prepare a detailed local development plan that includes socio-economic studies of residents living in the riverbank area before undertaking river and riverbank development work;
3. A detailed environmental development study to be prepared should include the development of a river corridor that takes into account the changes in landscape following the development of the river and riverbanks;
4. When developing a river and a riverbank, ensuring that it is uninterrupted from the upper part of the basin to the lower part of the river;
5. Notwithstanding the provisions of Sub Article (4) of this Article, carrying out development on any downstream part of the river as determined by the administration;
6. Together with the relevant administrative institution, identify the boundaries of the riverbank and issue a certificate of ownership from the relevant party; managing the sites; keep out;
7. Issuing a digital map of the river and riverbank areas and other green areas managed by the responsible management for the certificate of ownership;
8. According to the structural plan of the city administration, through the detailed environmental development studies prepared to implement the structural plan and parts plans, the riverbank areas and other green areas identified by collecting information from the relevant parties and making detailed designs are prepared and developed for them;

፱ የሚዘጋጁ የወንዝ ዳርቻ ዲዛይኖች የከተማ ፕላን ስታንዳደርዶችን ጠብቀው እንዲዘጋጁ እና በሚመለከተው አካል እንዲጸድቁ ማድረግ፤

፲ ለጎርፍ አደጋ የተጋለጡ የወንዝ ዳርቻዎችን በመለየት የከተማውን ውበት የሚያስጠብቁ እና ቀጣይ ልማት ታሳቢ የሚያደርጉ የተለያዩ የጎርፍ መከላከያ ስልቶችን በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግ፤

፲፩ ወንዞችና የወንዝ ዳርቻዎች በስታንደርዱና በዲዛይኑ መሠረት ፀድተውና ለምተው ለሕዝብ የመዝናኛና መናፈሻ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፤

፲፪ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የወንዞችና የወንዝ ዳርቻዎች ልማት ደረጃቸውን እና ጥራታቸው ተጠብቆ እንዲለሙ፣ የቴክኖሎጂ፣ የእውቀት እና የክህሎት ሽግግር እንዲኖር የማልማቱን ሥራ ለሀገር ውስጥ ወይም ለውጭ ኢንቨስተሮች አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ማስተላለፍ፤

፲፫ በተከለለ የወንዝ ዳርቻ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ነባር ልማት ባለበት ሁኔታ ሊቀጥል የሚችለው በወንዙና በወንዝ ዳርቻው ላይ ብዝሃ ህይወቱ ላይ ጉዳት ወይም ብክለት የማያስከትል መሆኑ አግባብ ባለው አካል ሲረጋገጥ ብቻ ይሆናል፤

፲፬ የወንዝና የወንዝ ዳርቻዎችን ሲለሙ የልማት ቅደም ተከተል በማውጣት፤

ሀ) የሚለማውን የወንዝና የወንዝ ዳርቻ ቦታዎችን በፕላን ቅደም ተከተልና በሕግ መሰረት ለልማት ተነሺዎች ካሳ እንዲከፈል እና ምትክ ቦታና ቤት ለሚያስፈልጋቸውም በሕግ መሠረት እንዲያገኙና የወሰን ማስከበር ሥራ እንዲሰራ ማድረግ፤

9. Ensuring that riverbank designs are prepared in accordance with urban planning standards and approved by the relevant body;
10. Designing and implementing different flood prevention strategies that protect the beauty of the city and take into account the continued development of riverbanks that are prone to flooding;
11. To make rivers and riverbanks clean according to the standard and design and provide recreational and park services to the public;
12. When necessary, transfer the development work to domestic or foreign investors in accordance with the relevant laws so that the development of rivers and riverbanks can maintain their level and quality, transfer technology, knowledge and skills;
13. Any existing development located in a protected riverbank can be continued in its current state only when it is confirmed by the appropriate body that it will not cause damage or pollution to the biodiversity of the river and the riverbank;
14. Establishing a development order when developing river and riverbanks:
    a) To ensure that compensation is paid to the developers of the developed river and riverside areas in accordance with the planning order and according to the law, and that those who need replacement places and houses can be found according to the law and that boundary enforcement work is carried out;

ለ) የወንዝ ዳርቻዎቹን ከማንኛውም ሕጋዊ የይገባኛል ጥያቄ ነጻ አድርጎ ለልማት ዝግጁ ማድረግ፤ እንደየአግባቡ መሰረተ ልማት በሟሟላት ወይም እንዲሟሉ በማድረግ ደረጃውንና ጥራቱን መሠረት አድርጎ እንዲለማ ማድረግ፤

ሐ) የወንዝ ዳር ልማት ከተጠናቀቀ በኋላ የወንዝ ኮሪደር ልማት በተዘጋጀው ዝርዝር የአካባቢ ልማት እቅድ መሰረት በሚመለከተው የመንግስት አካል የልማት እቅድ ተዘጋጅቶለት እንዲለማ ማድረግ፤

፲፭ በመንግሥትና በግል አጋርነት የሚለሙ የጋራ ፕሮጀክቶች ተጠንቶ በከንቲባ ሲወሰን አግባብ ባለው ሕግ መሠረት መፈጸም፤

፲፮ ነዋሪው በሚኖርበት፤ በሚሰራበት አካበቢ የሚገኝ የተፋሰስ አካል፤ የወንዝ እና የወንዝ ዳርቻን ማልማት፤ መንከባከብ፤ መጠበቅ ይኖርበታል፡፡

## ፭ ወንዝና የወንዝ ዳርቻ ከብክለት ስለመከላከል

፩ ወንዞችና የወንዝ ዳርቻዎች ከማንኛውም በካይ ነጻ ለማድረግ ግንዛቤ መፍጠር፤

፪ በወንዝ ዳርቻዎች ላይ ብክለትን የሚከላከሉ እና ውሃን የሚየፀዱ እጽዋት እንዲተከሉ ማድረግ፤

፫ በወንዝና በወንዝ ዳርቻ መጠበቂያ ቦታ ላይ ማንኛውም አካባቢን ሊበክል የሚችል ግንባታ እንዳይከናወን ማድረግ፤

፬ ከጤና ተቋማት፣ ከትምህርት ተቋማት፣ ከነዳጅ ማደያ፣ ከጋራዦች እና ከመኪና ማጠቢያዎች የሚወጡ የተለያዩ በካይ ኬሚካሎችን ፍሳሽ ወንዝና የወንዝ ዳርቻዎችን እንዳይበክሉ መቆጣጠር፤

b) Making the riverbanks free from any legal claims and ready for development; To develop the infrastructure based on its level and quality by completing it or making it complete as appropriate;

c) After the riverbank development is completed, the development of the river corridor should be developed by the relevant government body according to the detailed local development plan.

15. Joint projects developed by government and private partnership are studied and decided by the mayor to carry out in accordance with the relevant law;
16. Where the resident lives; a watershed component in the environment in which it operates; development of river and riverbanks; will have take care of it;

## 5. **Protection of River and Riverbanks from Pollution**

1. Creating awareness to make rivers and riverbanks free from any pollution;
2. Planting anti-pollution and water purification plants on riverbanks;
3. To prevent any construction that may pollute the environment in the river and river bank protection area;
4. Controlling the discharge of various pollutants from health institutions, educational institutions, gas stations, garages and car washes from polluting rivers and riverbanks;

፭ ከወንዝና ከወንዝ ዳርቻ ጋር ተያይዘው የተገነቡ እና ብክለት እያስከተሉ ያሉትን አገልግሎት መስጫ ተቋማት፣ መኖሪያ ቤቶችን እና አምራች ኢንዱስትሪዎች ከሚመለከታቸው የአስተዳደሩ አስፈጻሚ ተቋማት ጋር በመተባበር ከአካባቢው እንዲነሱ ወይም ተገቢ የሆነ የፍሳሽ ማጣሪያ ሥርዓት እንዲገነቡና የአሰፋፈር ማስተካከያ እንዲያደርጉ ማስቻል፤

፮ የከተማዋን የእድገት ደረጃ በሚመጥን መልኩ የወንዝ ብክለትን መከላከልና ማስወገድ የሚቻልበትን ሁኔታ መፍጠር፤

፯ ከማንኛውም ግለሰብ፣ መኖሪያ ቤት፣ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚመነጭ ቆሻሻ የወንዝ ብክለትን የሚያስከትል መሆን አለመሆኑን ቁጥጥር ማድረግ፤

፰ በወንዝና በወንዝ ዳርቻ ላይ ብክለትን የሚከላከል ቴክኖሎጂ መጠቀምን የሚያበረታታ እና የወንዝ ብክለትን ለማስወገድ የሚረዱ ፈጠራዎችን ማገዝ፤

፱ በወንዝ ዳርቻ አጠገብ የሚኖር ማንኛው ሰው ወንዙና የወንዝ ዳርቻውን የሚበክል ተግባር እንዳይፈጸም መከላከል፤

፲ ከኢንዱስትሪና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በካይ ንጥረ ነገር የያዙ ፍሳሾች ወደ ወንዝ እና ወንዝ ዳርቻ ከመለቀቃቸው በፊት የማጣራትና የማከም ተግባራት እንዲከናወኑ ማድረግ፤

፲፩ ማንኛውም ሰው ከሚያመርተው ቆሻሻ መልሶ በጥቅም ላይ ሊውል የሚችለውን ለይቶ በጥቅም ላይ እንዲያውል እና የወንዙ ጤንነት እንዲጠበቅ ማድረግ፤

5. Service facilities that have been built along the river and riverbanks and are causing pollution; Allowing residences and manufacturing industries to move out of the area in cooperation with the relevant executive institutions of the administration or to build an appropriate sewage treatment system and make settlement adjustments;
6. To create a situation where it is possible to prevent and eliminate river pollution in a way that suits the development level of the city;
7. To control whether the waste from any individual, residence, manufacturing and service-providing facilities causes river pollution;
8. Promote the use of anti-pollution technologies in rivers and riverbanks and support innovations that help to eliminate river pollution;
9. Preventing any person living near the river bank from doing activities that pollute the river and its banks;
10. To carry out screening and treatment activities before discharges containing pollutants from industrial and service facilities are released into rivers and riverbanks;
11. To ensure that the health of the river is protected by identifying and using what can be reused from the waste produced by everyone;

፲፪ ከጤና ተቋማት፣ ከትምህርት ተቋማት፣ ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና አምራች ድርጅቶች የሚወጡ የመጸዳጃ ቤት ፍሳሽን ወደ ባዮጋዝ በመቀየር ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ፤

፲፫ በወንዝ ተፋሰስ አካባቢ የሚገነባ የመጸዳጃ ቤት ፍሳሽ ማጠራቀሚያ አስተዳደሩ ባወጣው ስታንደርድና ጥራት መሠረት ብቻ እንዲገነባ ማድረግ፤

፲፬ የቆሻሻ ፍሳሽ መስመር ወይም ፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ከጎርፍ ውሃ ማስወገጃ መስመር ጋር እንዳይገናኝ መከላከል፡፡

**፮ የወንዝና የወንዝ ዳርቻዎችን ስለመንከባከብ**

የወንዝና የወንዝ ዳርቻ ልማትና እንክብካቤ የአካባቢ ማህበረሰብን በሚያሳትፍ እና ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ በቢሮው ታቅዶ እንዲተገበር ማድረግ፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የተከለከሉ ተግባራት እና ቁጥጥር

**፯ ክልከላ**

በወንዝና በወንዝ ዳርቻ ላይ የሚከተሉትን ተግባራት መፈጸም የተከለከለ ነው፡-

፩ ከጤና ተቋማት፣ ከትምህርት ተቋማት፣ ከነዳጅ ማደያ፣ ከጋራዦች እና ከመኪና ማጠቢያዎች የሚወጡ የተለያዩ በካይ ኬሚካል ፍሳሽ ቆሻሻዎችን በወንዝና ወንዙ ዳርቻ ላይ ማከማቸት ወይም መጣል ወይም መልቀቅ፤

፪ ከመኖሪያ ቤት፣ ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና አምራች ድርጅቶች የሚወጡ ተረፈ ምርቶች፣ የጠርሙስ ስብርባሪ፣ አገልግሎታቸውን የጨረሱ ጣሳዎች፣ ፕላስቲክና የፕላስቲክ ከረጢቶች፣ ያገለገሉ የተሸከርካሪ ጎማዎች፣ የሞተ እንስሳት አካል፤ በድን፤ አጥንት፤ ጸጉር፤ ቆዳ፤ የግንባታና የህንጻ ፍርስራሾች፣ ደረቅ ቆሻሻ እና ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸው በካዮች ወደ ወንዝና በወንዝ ዳርቻ መድፋት ወይም መጣል፤

12. Converting toilet waste from health institutions, educational institutions, service providers and manufacturing organizations into biogas for use;
13. To ensure that the toilet sewage tank built in the river basin area is built only according to the standards and quality issued by the administration;
14. Prevent sewage line or sewage tank from connecting to storm water drainage line.

6. **Taking Care of Rivers and Riverbanks**

To plan and implement the development and care of rivers and riverbanks in a manner that involves and benefits the local community; the detailed implementation will be determined by the guidelines issued by the Bureau.

## PART THREE

## PROHIBITED ACTIONS AND CONTROL

7. **Prohibition**

It is prohibited to perform the following activities on the river and riverbanks:

1. Accumulating or dumping or releasing various polluting chemical wastes from health institutions, educational institutions, gas stations, garages and car washes on the banks of the river;
2. Waste products from homes, service providers and manufacturing companies, broken bottles, used cans, plastic and plastic bags, used vehicle tires, dead animal carcasses; dead bone hair skin throwing or dumping construction and building debris, solid waste and other similar pollutants into rivers and riverbanks;

፫ ከመኖሪያ ቤት የሽንት ቤት ወይም ማንኛውም ያልተጣራ ፍሳሽ ቆሻሻ ወደ ወንዝ መልቀቅ ወይም መስመሩን አገናኝቶ ወንዙን መበከል፤

፬ ማንኛውንም ሰው ፈቃድ ሳይሰጠው የታከመ ፍሳሽን ወደ ወንዝ መልቀቅ፤

፭ ፍሳሽን ወደ ወንዝ ለመልቀቅ ፈቃድ ተሰጥቶት ቁጥጥር ሲደረግ የፍሳሽ የጥራት ደረጃዎች ሳያሟላ እና የተከለከሉ ይዘቶች፡-

ሀ) ከፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ ተጣርቶ ወደ ወንዝ የሚወጣ ፍሳሽ የጥራት ደረጃ በመቀነስ ወይም በማጓደል የሚለቀቅ ፍሳሽ፣

ለ) በራሱ ወይም ከሌላ ንጥረ ነገር ጋር በማዋሀድ መርዛማ ኬሚካል በማመንጨት በወንዙ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ፍሳሽ፣

ሐ) የፍሳሹ ፒኤች ከ፮ ያነሰ ወይም ከ፱ የሚበልጥ፣

መ) ከ፻ ዲግሪ ሴንቲግሬድ በታች በሆነ ሙቀት ሊተኑ የሚችሉ ነገሮችን በውስጡ የያዘ ፍሳሽ፣

ሠ) በወንዙ ውሃ ላይ የሚፈነዳ ወይም መርዛማና አደገኛ ጋዝ ወይም ትነት የሚያመነጭ ፍሳሽ፣

ረ) ዘይት፣ ጨዋማ ፈሳሽ፣ የተቀጣጠለ የሞተር ዘይት፣ ነዳጅ ወይም ሳሙና ነክ የሆኑ እና ሌሎች የወንዙን ውሃ ተፈጥሮዊ ይዘት ሊቀይሩ የሚችሉ ነገሮች የያዘ ፍሳሽ፣

ሰ) አትክልትና ፍራፍሬ ተረፈ ምርቶችን፣ እንጨት፣ ጠጠር፣ አሸዋ፣ ጨርቅ፣ ድንጋይ የመሳሰሉትን በውስጡ የያዘ ፍሳሽ፤

3. Discharge sewage from residential toilets or any untreated sewage into a river or pollute the river by connecting the line;

4. Discharge treated sewage into a river without the consent of any person;

5. When a permit is issued to discharge sewage into a river and it is controlled, the effluent does not meet the quality standards and has prohibited contents:

   a) Sewage that is discharged from the sewage treatment plant and discharged into the river by reducing or degrading the quality level;

   b) Sewage that harms the river by generating toxic chemicals by itself or by mixing with other substances;

   c) PH of effluent less than 6.0 or greater than 9.0;

   d) Effluent containing substances that can evaporate at temperatures below 100 degrees Celsius;

   e) Leakage that explodes on the river water or produces poisonous and dangerous gas or vapor;

   f) Drainage containing oil, salty liquid, burning motor oil, petrol or soapy substances and other substances that may change the natural composition of the river water;

   g) Sewage containing vegetable and fruit by-products, wood, gravel, sand, cloth, stone, etc.;

፮. ማንኛውም በካይ ፍሳሽ ከተፈቀደው የፍሳሽ ማጠራቀሚያ ወይም የፍሳሽ መስመሩን ወደ ወንዝ ወይም የፍሳሽ መስመሩን ከጎርፍ መውረጃ ቦይ ጋር በማገናኘት ወደ ወንዝና ወንዝ ዳርቻ እንዲፈስ ማድረግ፤

፯. ኬሚካል ነክ ፍሳሾችን ተገቢውን የማከሚያ ዘዴ ሳይጠቀሙና ባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ያለው አካል ሳያረጋግጥ ወደ ወንዝና ወንዝ ዳርቻ መድፋት ወይም መልቀቅ፤

፰. ከአምራችና አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ማንኛውንም ያልታከመ ፍሳሽ ቆሻሻ ወደ ወንዝ በመልቀቅ ወይም መስመሩን ማገናኘት መበከል፤

፱. የሽንት ቤት ፍሳሽ የማስወገድ ፈቃድ ወስዶም ሆነ ፈቃድ ሳይወስድ የሚሰራ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት በሚያስወግድበት ጊዜ ቀጥታ ወደ ወንዝ በመድፋት ወይም መቀላቀል፤

፲. በባህሪው አደገኛነት ያለው ደረቅም ሆነ ፍሳሽ ቆሻሻ ወደ ወንዝ መጣል ወይም እንዲጣል በማድረግ መበከል፤

፲፩. በወንዝና በወንዝ ዳርቻ ክልል ውስጥ መጸዳዳት፤

፲፪. የፍሳሽ ማጣሪያ ሳይኖረው በወንዝ ዳርቻ እና አካባቢ ላይ የተሽከርካሪ እጥበት ማከናወን፤

፲፫. በወንዝ ዳርቻ ክልል ውስጥ እንስሳት ማሰማራት ወይም እንዲገቡ ማድረግ ወይም ከተፈቀደ መግቢያና መውጫ ውጭ ተሽከርካሪ ማሽከርከር፤

፲፬. በወንዝና በወንዝ ዳርቻ ውስጥ ከተፈቀደው የመዝናኛ፣ መናፈሻና፣ ፓርክ እና ሌሎች ለወንዝ ዳርቻው ልማት አስፈላጊ ከሆነ ግንባታ ውጭ የፕላስቲክ ቤት ወይም ማንኛውም ዓይነት ግንባታ መገንባት፡፡

6. Any pollutant discharge from an approved septic tank or sewer line to a river or by connecting the sewer line to a flood drain to flow to a river or riverbank;

7. Throwing or releasing chemical spills into rivers and riverbanks without using appropriate treatment methods and without being verified by the authority or appropriate body;

8. Contamination by releasing any untreated sewage from manufacturing and service-providing facilities into a river or connecting the line;

9. Any individual or organization operating with or without a permit to dispose of toilet waste discharges it directly into the river or mixes it;

10. Disposing of hazardous solid or sewage waste into a river or polluting it by dumping;

11. Defecating in rivers and riverbank areas;

12. Carrying out vehicle washing in and around riverbanks without sewage treatment;

13. Grazing or allowing animals to enter the riverbank zone or driving a vehicle outside the authorized entrance and exit;

14. Constructing a plastic house or any type of construction outside of the permitted recreation, amusement park, park and other construction necessary for the development of the river bank in the river and riverbanks.

**፰. <u>የወንዝና የወንዝ ዳርቻ ተቆጣጣሪ</u>**

፩. በዚህ ደንብ መሰረት በወንዝና በወንዝ ዳርቻ ውስጥ የተከለከለ ድርጊት እንዳይፈጸም ወይም የወንዝና የወንዝ ዳርቻ ብክለትን የሚከላከል ተቆጣጣሪ በባለሥልጣኑ ሊመደብ ይችላል፤

፪. ተቆጣጣሪዎች በዚህ ደንብ መሠረት ሥልጣንና ተግባራቸውን ሲወጡ ሥራቸውን በትጋት፣ በታማኝነትና ያለአድልዎ መፈጸም አለባቸው፡፡

**፱. <u>የወንዝና ወንዝ ዳርቻ ተቆጣጣሪ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

ተቆጣጣሪው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

፩. የወንዝ ወይም የወንዝ ዳርቻን ሊበክል ይችላል ብሎ የጠረጠረውን የማንኛውንም ነገር የተመጠነ ናሙናን ለባለንብረቱ ወይም ለወኪሉ በጽሁፍ አሳውቆ የመውሰድ እና ጉዳት የሚያደርስ መሆን አለመሆኑን በላብራቶሪ ይመረምራል ወይም ያስመረምራል፤

፪. የወንዝና ወንዝ ዳርቻ ብክለት መከታተያ መዝገቦች፣ ሰነዶች፣ ወይም ሌሎች ተያያዥ መረጃዎች እንዲቀርቡለት ይጠይቃል፣ ይመረምራል፣ ቅጅ ይወስዳል፤

፫. የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች መተላለፉን በማስረጃ ያረጋገጠበትን ሰው ለጥያቄ ወደ ባለስልጣኑ እንዲመጣ መጥሪያ ይሰጣል፤

፬. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የወንዝና ወንዝ ዳርቻ ብክለት ባለበት ቦታ ተገኝቶ ምልከታ ያደርጋል፤ሪፖርት ያዘጋጃል፤ ለበላይ ኃላፊው ያቀርባል፤

፭. ለቁጥጥር ስራ በሚሰማራበት ጊዜ መታወቂያ ያሳያል፤

**8. <u>River and Riverbank Inspector</u>**

1. According to this regulation, an inspector may be assigned by the authority to prevent prohibited activities in the river and riverbanks or to prevent river and riverbank pollution;
2. In exercising their powers and duties under this regulation, inspectors shall perform their duties diligently, honestly and impartially.

**9. <u>Duties and Responsibilities of Riverbank Inspector</u>**

The inspector will have the following duties and responsibilities:

1. Notify the owner or his agent in writing of taking a measured sample of any substance which he suspects may contaminate the river or riverbank and examine or have it tested by a laboratory to determine whether it is harmful;
2. Requests, examines, and takes copies of riverbank pollution monitoring records, documents, or other related information;
3. He shall issue a summons to the person whom he has proven to have violated the provisions of this regulation to come to the authority for questioning;
4. When it is necessary, he will be present at the place where there is pollution along the riverbank and will make observations and prepare a report. Submits to the superior officer;
5. Displays ID when deployed for control;

፮ ተቆጣጣሪው በዚህ ደንብ የተደነገጉ ጥፋቶች መፈጸማቸውን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን በተለያየ ዘዴ ያደራጃል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ያስረዳል፤

፯ የዚህን ደንብ አላማዎችና ድንጋጌዎች ለማስፈጸምና ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ክፍል አራት

## የተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

**፲ የቢሮው ተግባርና ኃላፊነት**

አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

፩ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ እና ፮ የተደነገጉ መርሆዎችና የወንዝና የወንዝ ዳርቻ እንክብካቤን በተመለከተ ከባለድርሻ እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀትና በማስተባበር በኃላፊነት ያስተገብራል፤

፪ የወንዝ ዳርቻ አከላለል፣ ልማት እና እንክብካቤ የአተገባበር ማኑዋል ያዘጋጃል፤ ያሰራጫል፤

፫ ውጤታማ እና ዘላቂ የሆነ የወንዝና የወንዝ ዳርቻ ልማት እና እንክብካቤ ተግባራት አፈጻጸም የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ይዘረጋል፤

፬ የወንዝና የወንዝ ዳርቻዎች እንዲለሙ ያደርጋል፤ ይንከባከባል፤ ይጠብቃል፤ ያስጠብቃል፤

፭ አግባብነት ያላቸውን አካላት በማስተባበርና አስፈላጊውን የሙያ ድጋፍ በመስጠት ይህን ደንብ ያስፈጽማል፤

፮ በወንዝና በወንዝ ዳርቻ ልማት፣ ይዞታ ላይ ሕገ-ወጥ ድርጊት መፈጸሙ ከነዋሪዎች ጥቆማ ሲቀርብ ይቀበላል፤ ያጣራል፤ መፍትሔ ይሰጣል፤



6. The inspector shall arrange the evidence of the offenses stipulated in this regulation in different ways; explains when necessary;

7. Performs other duties necessary to enforce and ensure the objectives and provisions of this regulation.

## PART FOUR

## DUTIES AND RESPONSIBILITIES OF INSTITUTIONS

10. **The Duties and Responsibility of the Bureau**

Subject to the power and duties given by the relevant laws, it shall have the following duty and responsibilities:

1. It applies the principles set forth in Article 4 and 6 of this regulation and the care of the river and the riverbank in coordinating and cooperating with the stakeholders and the relevant parties;
2. Develops an implementation manual for riverbank zoning, development and care; it distributes.
3. A monitoring and evaluation system will be developed for effective and sustainable river and riverbank development and maintenance activities;
4. It will develop the river and riverbanks; it maintain; it keep out; it protects;
5. It enforces this regulation by coordinating the relevant bodies and providing the necessary professional support;
6. It receives suggestions from residents about illegal activities in river and river bank development and possession; it filters, it provides a solution;

፯. የወንዝና የወንዝ ዳርቻ ልማት፣ ክብካቤ እና ጥበቃ ላይ ከሚሠሩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት በትብብር ይሰራል፤

፰. በወንዝ ዳርቻ ውስጥ ለልማት የሚፈቀዱና የማይፈቀዱ ተግባራትን ይወስናል፤ በውሳኔው መሠረት ያስፈጽማል፤

፱. ስለወንዝና የወንዝ ዳርቻ ልማት፣ ክብካቤና ጥበቃ ለነዋሪዎች እና ለሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት ግንዛቤ ይፈጥራል ወይም እንዲፈጠር ያደርጋል፤

፲. በወንዝና በወንዞች ዳርቻ ልማት፣ ይዞታ እና ጥበቃ ላይ ለሚደርስ ጉዳት ወይም በወንዞች ላይ ደረቅ ቆሻሻ ወይም ፍሳሽ ሲጣል ወይም ሲደፋ ወይም ሲለቀቅ ወይም እንዲለቀቅ ሲደረግ ወይም ሲከማች ወይም ሲጣል በድርጊት ፈጻሚው ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ከሚመለከተው አካል ጋር በትብብር ይሰራል፡፡

**፲፩ <u>የባለሥልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ የተደነገጉ የመከላከያ ስልቶችን ተከትሎ የወንዝና የወንዝ ዳርቻ ብክለትን ከባለድርሻ እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀትና በማስተባበር ይከላከላል፤

፪. በህግ መሰረት የተመዘገቡና ፈቃድ ያገኙ አገልግሎት ሰጪ እና አምራች ተቋማት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ደንብ እና በዚህ ደንብ መሠረት አክብረው መስራታቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል

7. It works in cooperation with governmental and non-governmental organizations working on the development, care and protection of rivers and riverbanks in accordance with relevant laws;

8. Determines what is allowed and what is not allowed for development in the river bank; it executes according to the decision;

9. Creates or will create awareness for residents and other interested parties about the development, care and protection of rivers and riverbanks;

10. It works in cooperation with the relevant party to take action against the perpetrators of damage to the development, ownership and protection of rivers and riverbanks, or when solid waste or sewage is dumped or dumped or released or is released or stored or dumped.

11. **<u>Duties and Responsibilities of the Authority</u>**

Subject to the power and duties given by the relevant laws, it shall have the following duties and responsibilities:

1. Following the prevention strategies stipulated in Article 5 of this regulation, it prevents river and riverbank pollution by organizing and coordinating with stakeholders and relevant bodies;

2. The Addis Ababa City Administration monitors the environmental pollution control regulation of the registered and licensed service providers and production facilities in accordance with this regulation;

፫ የወንዝና ወንዝ ዳርቻ ብክለትን የሚመለከቱ መዝገቦች፣ ሰነዶች፣ ወይም ሌሎች ተያያዥ መረጃዎች እንዲቀርቡለት ይጠይቃል፣ ይመረምራል፣ ቅጅ ይወስዳል፤

፬ ከወንዝና የወንዝ ዳርቻ የፍሳሽ ወይም ቁሶችን ናሙና ይወስዳል፤ ናሙናውንም በላቦራቶሪ እንዲመረመር ያደርጋል፤ የምርመራውን ውጤት መሠረት አድርጎ እርምጃ ይወስዳል፤

፭ የወንዝና የወንዝ ዳርቻ ቦታዎች ለታለመላቸው ዓላማ ብቻ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፮ ማንኛውም ሰው ወደ ወንዝና ወንዝ ዳርቻ የሚለቀው ፍሳሽ ብክለት የማያስከትል መሆን አለመሆኑን ቁጥጥር ያደርጋል፤

፯ በወንዝ ብክለት ምክንያት የደረሰውን ጉዳት በካዩ ወደ ቀድሞ ሁኔታ የሚመልስበትን የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤

፰ የዚህን ደንብ አላማዎችና ድንጋጌዎች ለማስፈጸምና ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**፲፪ <u>የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ተግባርና ኃላፊነት</u>**

አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

፩ በወንዝና ወንዝ ዳርቻ ልማት እና ይዞታ ላይ ለሚደርስ ጉዳት ወይም ደረቅ ቆሻሻ ወይም ፍሳሽ ሲጣል ወይም ሲደፋ ወይም ሲለቀቅ ወይም እንዲለቀቅ ሲደረግ ወይም ሲከማች በድርጊት ፈጻሚው ላይ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፪ ከባለሥልጣኑ ብክለት መኖሩ ሲረጋገጥና እና ሲቀርብለት በዚህ ደንብ አባሪ ሰንጠረዥ መሠረት አስተዳደራዊ የገንዘብ መቀጫ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

3. It controls requests, examines, and takes copies of records, documents, or other related information related to riverbank pollution;

4. Takes samples of effluent or materials from rivers and riverbank; it will also have the sample analyzed in a laboratory; actions will be taken based on the results of the investigation;

5. Monitors that river and riverbank areas are used only for their intended purpose; it controls;

6. Any person shall control whether the effluent discharged into the river and riverbank is not polluting;

7. Develops a system of procedures to restore the damage caused by river pollution;

8. Performs other duties necessary to enforce and ensure the objectives and provisions of this regulation.

**12. <u>Duties and Responsibilities of Code Enforcement Authority</u>**

Subject to the power and duties given by the relevant laws, it shall have the following duties and responsibilities:

1. Takes action against the perpetrator of the action or causes it to be taken for the damage caused to the development and ownership of the riverbank or when solid waste or sewage is dumped or dumped or released or caused to be released or stored;

2. When the presence of pollution is confirmed and presented to the authority, it will apply an administrative fine according to the table attached to this regulation.

፲፫ **መንገዶች ባለሥልጣን**

አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

፩ ከማንኛውም መኖሪያ፣ አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የሚወጣ ፍሳሽ ቆሻሻ ወደ ጎርፍ ማስወገጃ መስመር እንዳይገባ ይቆጣጠራል፤ ይከላከላል፤ ጥፋት ፈጽሞ የተገኘውን ማስረጃ በማደራጀት ለደንብ ማስከበር ባለሥልጣን መረጃውን ያስተላልፋል፤

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ወደ ጎርፍ ማስወገጃ መስመር የተለቀቀ ፍሳሽ የበካይነትና አደገኛነት ደረጃ እንዲጣራ ለአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ጥቆማ ያቀርባል፡፡

፲፬ **እውቅና እና ማበረታቻ ስለመስጠት**

ባለሥልጣኑ የተበከለን ወንዝና የወንዝ ዳርቻ በማጽዳትና በመንከባከብ አርአያነት ያለው ተግባር ለፈጸሙ ግለሰቦች፤ ድርጅቶች፤ ሲቪል ማህበራት እና ተቋማት እውቅናወይም ማበረታቻ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**ክፍል አምስት**

**ጥቆማና አቤቱታ ስለመቀበልና ቅንጅታዊ አሰራር**

፲፭ **ጥቆማና አቤቱታ ስለማቅረብ**

፩ ማንኛውም ሰው የወንዝ ወይም በወንዝ ዳርቻ ብክለት አድርሷል ወይም ሊደርስ ይችላል የሚል ጥቆማ ወይም አቤቱታ ለባለስልጣኑ በአካል በማቅረብ፣ በጽሁፍ፣ በስልክ እንዲሁም በሌላ የኤሌክትሮኒክስ መልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴዎች ማቅረብ ይችላል፤

13. **Roads Authority**

Subject to the power and duties given by the relevant laws, he shall have the following duties and responsibilities:

1. Controls sewage from any residential, manufacturing or service-providing company to prevent it from entering the flood drainage line; it protects; organizes the evidence of crime and transfer the information to Code Enforcement Authority;
2. According to Sub Article (1) of this Article, it makes a recommendation to the Environmental Protection Authority to check the level of pollution and danger of the sewage released into the flood drainage line.

14. **Giving Recognition and Encouragement**

The authority to individuals who have done exemplary work in cleaning and maintaining polluted rivers and riverbanks; organizations; civil societies and institutions may be recognized or encouraged.

**PART FIVE**

**ACCEPTING SUGGESTION, PETITION AND COORDINATING PROCEDRES**

15. **Submitting Suggestion and Petition**

1. Any person who has caused or may cause pollution of the river or the riverbank can submit a suggestion or petition to the authority by presenting it in person, in writing, by telephone or by other means of electronic message transmission;

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የሚቀርብ ጥቆማ ወይም አቤቱታ በካዩ የተለቀቀበትን ወይም የተጣለበትን ወንዝ ወይም የወንዝ ዳርቻ ትክክለኛውን ቦታ ወይም አድራሻ፣ ከተቻለ በካይ ነገሩ መለቀቅ የጀመረበት ጊዜ፣ የሚለቀቀውን የበካይ ዓይነት፣ የሚለቀቅበትን ጊዜ የሚገልጽ ሊሆን ይችላል፤

፫. አቤቱታ ወይም ጥቆማ የሚቀርበበት ቅጽ ባለስልጣኑ ያዘጋጃል፤

፬. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ ቢኖርም አቤቱታ አቅራቢው አመቺ በሆነ መንገድ ጥቆማውን ወይም አቤቱታውን ሊያቀርብ ይችላል፤

፭. ጠቋሚው ወይም አቤት ባዩ ያቀረበውን ጥቆማ ወይም አቤቱታ አፈጻጸም መከታተል፣ ውጤቱንም ማወቅ ይችላል፤

፮. በወንዝና በወንዝ ዳርቻ ልማት ላይ ጉዳት ሲደርስ ወይም ሊደርስ ይችላል የሚል ጥቆማ ወይም አቤቱታ ያለው ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ መሠረት ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ማቅረብ ይችላል፡፡

**፲፮ ቅንጅታዊ አሰራር**

፩. ባለሥልጣኑ ከወንዝና ወንዝ ዳርቻ ብክለት ጋር በተገናኘ ከሚመለከታው አካል ጋር በትብብርና በቅንጅት ይሰራል፤

፪. ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ የተደነገጉ ክልከላዎች እና አስተዳደራዊ እርምጃዎችን አፈጻጸምና አተገባበር ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ጋር በትብብርና በቅንጅት ይሰራል፤

2. A suggestion or petition submitted in Sub Article (1) of this Article may specify the exact location or address of the river or riverbank where the pollutant was released or dumped, if possible, the time the pollutant began to be released, the type of pollutant released, and the time it was released;

3. The authority will prepare a form to submit a petition or suggestion;

4. Notwithstanding the provisions of Sub Article (3) of this Article, the petitioner may present his suggestion or petition in any convenient manner;

5. To monitor the implementation of the suggestion or petition submitted by the indicator or petitioner; he can know the result;

6. Any person who has a suggestion or a petition that there is or may be damage to the development of the river and riverbank can submit it to the Addis Ababa city Administration's Code Enforcement Authority in accordance with this Article.

16. **<u>Coordinating Procedure</u>**

1. The Authority will work in cooperation and coordination with the relevant body in relation to river and riverbank pollution;

2. The Authority shall work in cooperation and coordination with the Addis Ababa City Administration's Code Enforcement Authority in the implementation and enforcement of the prohibitions and administrative measures stipulated in this regulation;

፫ ባለስልጣኑ በአስተዳደሩ የሚከሰቱ ወይም ሊከሰቱ የሚችሉ የወንዝና የወንዝ ዳርቻ ብክለቶችን ለመከላል ከከተማው አዋሳኝ ክልል ጋር በመተባበር ይሰራል፤

፬ ቢሮው በወንዝና በወንዝ ዳርቻ ልማት እና ክብካቤ በተመለከተ አግባብነት ካላቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በትብብርና በቅንጅት ይሰራል፡፡

## ክፍል ስድስት
## አስተዳደራዊ እርምጃ

### ፲፯ ስለአስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድ

፩ በወንጀል ሕግ እና በሌሎች ሕጎች የተመለከተው ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ እንደአግባብነቱ ባለሥልጣኑ ወይም የከተማው አስተዳደር የደንብ ማከበር ባለሥልጣን ይህንን ደንብ በተላለፈ ማንኛውንም ሰው ላይ፡-

ሀ) እንደ ጥፋቱ ሁኔታ ድርጊቱን የማስቆም፣ የማዘጋት፣ የማሸግ፣ ወደነበረበት ቦታ እንዲመለስ የማድረግ፣ የንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም የግንባታ ፈቃድ እንዲሰረዝ የማድረግ፣ የውሃ አቅርቦት እንዲቋረጥ ስልጣን ላላቸው ተቋማት በጽሑፍ የማሳወቅ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፤

ለ) በዚህ ደንብ አባሪ በተደረገው ሰንጠረዥ መሰረት አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፤

፪ ባለሥልጣኑ የወንዝና የወንዝ ዳርቻ ብክለት እንዳይኖር ወይም ብክለት የሚያስከትል ተግባር እንዲቆም ወይም ብክለት ሊያስከትል የሚችለው ነገር እንዳይመረት ወይም ከቦታ ቦታ እንዳይንቀሳቀስ ወይም በአግባቡ እንዲወገድ ወይም በጥንቃቄ እንዲያዝ ውሳኔ ይሰጣል፤

3. The Authority works in cooperation with the bordering region of the city to prevent river and riverside pollution caused or likely to occur by the administration;

4. The Bureau works in cooperation and coordination with relevant governmental and non-governmental organizations regarding the development and care of rivers and riverbanks.

## PART SIX
## ADMINISTRATIVE ACTION

### 17. Taking Administrative Action

1. Subject to the penalties provided for in the Penal Code and other laws, the appropriate authority or city government Code Enforcement Bureau shall impose upon any person who violates this regulation:

   a) According to the nature of the offense, it will take administrative action to stop, close, seal, restore, cancel business license or construction license, notify the authorities in writing to cut off water supply;

   b) An administrative fine shall be imposed according to the table attached to this regulation;

2. The authority makes a decision to ensure that there is no pollution of the river and the riverbank, or to stop activities that cause pollution, or to prevent the production or movement of things that may cause pollution, or to dispose of them properly or order them carefully;

፫ ባለሥልጣኑ በግለሰቦች ቦታ ላይ የፈሰሰ ወይም የተከማቸ በካይ ነገር በዝናብ ተጠርጎ ወደ መንገድ፣ ወንዝ ወይም ጎርፍ መውረጃ ቦይ እንዳይገባ ለመከላለከል የሚያስችሉ አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ዝግጅቶችን እንዲያደርግ ለባለንብረቱ ትዕዛዝ ይሰጣል፤

፬ በደንብ ማስከበር ባለሥልጣን በዚህ ደንብ መሠረት አስተዳደራዊ ቅጣት የተጣለበት ማንኛውም ሰው የተሰጠውን አስተዳደራዊ ቅጣት ማስታወቂያ ወረቀት በመያዝ ወዲያውኑ ጥፋቱ በተፈፀመበት አካባቢ በሚገኘው የወረዳው ደንብ ማስከበር ጽህፈት ቤት ቀርቦ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መክፈያ ዘዴ በሶስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣቱን ገቢ በማድረግ ቅጣቱን መፈጸም አለበት፤

፭ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የበከለውን አካባቢ ወይም ወንዝና የወንዝ ዳርቻ ከብክለቱ በፊት ወደነበረበት በራሱ ወጪ እንዲመልስ እና በሰዎች ወይም በጥቅሞቻቸው ላይ ብክለቱ ያደረሰውን ጉዳት የመካስ ኃላፊነት አለበት፤

፮ የቅጣት ማስታወቂያ ለመቀበል ፍቃደኛ ካልሆነ እንደተቀበለ ተቆጥሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) ድንጋጌ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

፯ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት አስተዳደራዊ መቀጫውን ገቢ ያላደረገ ሰው የተጣለበትን የቅጣት መቀጫ መጠን እጥፍ እንዲከፍል ይደረጋል፤

፰ እንደጥፋቱ ክብደት እና እንደፈጻሚው ግንዛቤ ደረጃ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ደንብ ተላላፊው የፈጸመውን ጥፋት እና የተወሰነበትን አስተዳደራዊ ቅጣት በመገናኛ ብዙሃን ለህዝብ ይፋ ሊያደረግ ይችላል፤

3. The authority shall order the owner to make necessary arrangements to prevent any pollutant spilled or accumulated on private property from being washed away by rain and entering the road, river or drainage ditch;

4. Any person to whom an administrative fine has been imposed by the Code Enforcement Bureau according to this regulation must immediately present himself at the district Code Enforcement Office in the area where the offense occurred with the given administrative fine notice or pay the administrative fine within three consecutive working days by electronic payment method;

5. Subject to the provisions of Sub Article (4) of this Article, he shall be responsible for restoring the planted area or the river and riverbank to its condition before the pollution at his own expense and to compensate the damage caused by the pollution to people or their interests;

6. If he refuses to accept the penalty notice, he shall be deemed to have received it and shall be enforced in accordance with the provisions of Sub Article (7) of this Article;

7. According to Sub Article (4) of this Article, a person who does not pay the administrative fine will be made to pay double the amount of the fine imposed;

8. When it is necessary according to the severity of the offense and the level of awareness of the offender, the Code Enforcement Authority may publicize the offense committed by the violator and the administrative fine imposed through the media.

፱ በዚህ ደንብ የተደነገጉ ጥፋቶች መፈጸማቸውን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን በተለያየ ዘዴ የማደራጀት እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማስረዳት ኃላፊነት አለበት፤

፲ የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) መሠረት መቀጫውን ገቢ ያላደረገ ማንኛውም ሰው አስተዳደራዊ ቅጣቱን ለማስፈጸም ለከተማው አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ይልካል፡፡

**፲፰ ስለተደጋጋሚ ጥፋትና አስተዳደራዊ ቅጣት**

ማንኛውም ይህንን ደንብ በመተላለፍ አስተዳደራዊ ቅጣት የተወሰነበትን ቅጣት ከፈጸመበት ቀን ጀምሮ በድጋሚ ተመሳሳይ ጥፋት የፈፀመ እንደሆነ፡-

፩ በዚህ ደንብ በቅጣት ሰንጠረዥ የተገለጸውን አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት እጥፍ ይከፍላል፤

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) የንግድ ሥራ የሚያከናውን ከሆነ የንግድ ሥራ ፈቃድ ይሰረዛል፤ የውሃ አቅርቦት ይቋረጣል፣

ለ) መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት፣ መኖሪያ ቤት፣ የማምረቻ ተቋም፣ የትምህርት ተቋም፣ የጤና ተቋም፣ ገራዥ ወይም መኪና ማጠቢያ ከሆነ የውሃ አቅርቦት ይቋረጣል፤

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት ክፍያውን ካልፈጸመ ወይም ግዴታውን ካልተወጣ ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ በመመስረት ክፍያውን እንዲከፍል ወይም ግዴታውን እንዲወጣ ይደረጋል፤

9. He is responsible for organizing the evidence that proves the commission of the offenses stipulated in this regulation in different ways and explaining it when necessary;

10. The Code Enforcement Bureau shall send any person who does not pay the fine according to Sub Article (7) of this Article to the City Administration Justice Bureau to enforce the administrative fine.

18. **Repeated Fault and Administrative Fine**

Any person who violates this regulation and commits the same fault again from the date of serving the administrative fine:

1. Shall pay double the administrative fine specified in the table of penalties in this regulation;

2. Subject to the provisions of Sub Article (1) of this Article:

   a) Business license will be revoked if he is doing business; water supply will be cut off;

   b) If it is a governmental or non-governmental organization, residence, manufacturing facility, educational facility, health facility, garage or car wash, water supply will be cut off;

3. According to Sub Articles (1) and (2) of this Article, if he does not make the payment or does not fulfill his obligation, he will be made to pay the payment or fulfill his obligation based on a case to the competent court in cooperation with the relevant body;

፬ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተራ ፊደል (ሀ) እና (ለ) መሠረት አስተዳደራዊ እርምጃ የተወሰደበት ማንኛውም ሰው ቅጣቱን ሲከፍል እና ድርጊቱን ሲያቆም ወይም ቅጣቱ ቀሪ ሲሆን የተሰረዘው ንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም የተቋረጠው የውሃ አገልግሎት ወደ ነበረበት እንዲመለስ ለሚመለከተው አካል በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

## ክፍል ሰባት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲፱ የመተባበር ግዴታና ተጠያቂነት**

፩ ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ የተከለከሉ ድርጊቶች መፈጸማቸውን ካወቀ ለባለስልጣኑ ወይም ለደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ወይም ለቢሮው የመጠቆም ግዴታ አለበት፤

፪ ማንኛውም ሰው ለወንዝና ለወንዝ ዳርቻ ተቆጣጣሪ ወይም ለደንብ ማስከበር ኦፊሰር መረጃ የመስጠት እና ተግባሩን ሲያከናውን የመተባበር ግዴታ አለበት፤

፫ ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ በመተላለፍ ኃላፊነቱን ባለመወጣት ወይም የዚህን ደንጋጌዎች በመጣስ ለሚፈፀም ጥፋት እንደአስፈላጊነቱ በወንጀል፣ በፍትሐብሔር እና/ወይም በአስተዳደር ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**፳ ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች**

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም የከተማ ካቢኔ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም

**፳፩ ደንቡ ስለሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከታህሳስ ፬ ቀን / ፪ሺ፲፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፬ ቀን / ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

4. Any person who has been subject to administrative action according to Sub Article (2) of this Article shall pay the fine and stop the action or when the penalty remains, he shall notify the relevant body in writing to restore the revoked business license or the interrupted water service.

## PART SEVEN
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

19. **Duty to Cooperate and Accountability**

1. If any person discovers that any act prohibited by this regulation has been committed, he is obliged to report it to the authority or the Code Enforcement Bureau or the Bureau;
2. Every person has a duty to provide information to and cooperate with a river and riverbank Inspector or Code Enforcement Officer;
3. Any person, who violates this regulation, fails to fulfill his responsibilities or commits fault in violation of these provisions shall be criminally, civilly and/or administratively accountable, as appropriate;

20. **Inapplicable Laws**

Any regulation, directive or customary practice of the City Cabinet which are inconsistent with this Regulation shall have no effect.

21. **Effective Date**

This Regulation shall enter into force as of this 13th day of December, 2024.

**Done at Addis Ababa, this 13th day of December 2024.**

**Adanech Abiebie Des**

**Mayor of Addis Ababa City**

## ሠንጠረዥ 1

## የወንዝና የወንዝ ዳርቻ ብክለት አሰተዳዳራዊ የገንዘብ ቅጣት

| ተ.ቁ | በወንዝና በወንዝ ዳርቻ ላይ የሚፈጸም የብክለት ወይም የጥፋት ዓይነት | የቅጣት መጠን በገንዘብ |
|---|---|---|
| ፩ | ከጤና ተቋማት፣ ከትምህርት ተቋማት፣ ከነዳጅ ማደያ፣ ከጋራዦች እና ከመኪና ማጠቢያዎች የሚወጡ የተለያዩ በካይ ኬሚካል ፍሳሽ ቆሻሻዎችን በወንዝና ወንዙ ዳርቻ ላይ ማከማቸት ወይም መጣል ወይም መለቀቅ፤ | ብር ፬፻ሺህ |
| ፪ | ከመኖሪያ ቤት፣ ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና አምራች ድርጅቶች የሚወጡ ተረፈ ምርቶች፣ የጠርሙስ ስብርባሪ፣ አገልግሎታቸውን የጨረሱ ጣሳዎች፣ ፕላስቲክና የፕላስቲክ ከረጢቶች፣ ያገለገሉ የተሽከርካሪ ጎማዎች፣ የሞተ እንስሳት አካል፤ በድን፤ አጥንት፤ ጸጉር፤ ቆዳ፤ የግንባታና የህንጻ ፍርስራሾች፣ ደረቅ ቆሻሻ እና ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸው በካዮች ወደ ወንዝና በወንዝ ዳርቻ መድፋት ወይም መጣል፤ | • ለግለሰብ ብር ፳ሺህ<br>• ለድርጅት ብር ፻ሺህ |



## Table 1

## Administrative Fines for Pollution of Rivers and Riverbanks

| No. | Type of Pollution or Fault takes place in the river and on the banks of the river | Amount of Fine in money |
|---|---|---|
| 1 | Accumulation or dumping or release of various polluting chemical wastes from health institutions, educational institutions, gas stations, garages and car washes on the banks of the river; | 400,000.00 Birr |
| 2 | Waste products from homes, service providers and manufacturing companies, broken bottles, used cans, plastic and plastic bags, used vehicle tires, dead animal carcasses; dead bone hair skin throwing or dumping construction and building debris, solid waste and other similar pollutants into rivers and riverbanks; | • 20,000.00 Birr for an individual<br>• 100,000.00 Birr for organization |

| | | |
|---|---|---|
| ፫ | ከመኖሪያ ቤት የሽንት ቤት ወይም ማንኛውም ያልተጣራ ፍሳሽ ቆሻሻ ወደ ወንዝ የለቀቀ ወይም መስመሩን አገናኝቶ ወንዙን የበከለ፤ | • ለግለሰብ ብር ፻፶ሺ.ህ<br>• ለድርጅት ብር ፫፻ ሺ.ህ |
| ፬ | ማንኛውንም ሰው ፈቃድ ሳይሰጠው የታከመ ፍሳሽን ወደ ወንዝ መልቀቅ፤ | • ለግለሰብ ብር ፲፭ሺ.<br>• ለድርጅት ብር ፵ሺ.ህ |
| ፭ | ፍሳሽን ወደ ወንዝ ለመልቀቅ ፈቃድ ተሰጥቶት ቁጥጥር ሲደረግ የፍሳሽ የጥራት ደረጃዎች ሳያሟላ እና የተከለከሉ ይዘቶች፡- | |
| | ሀ) ከፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ ተጣርቶ ወደ ወንዝ የሚወጣ ፍሳሽ የጥራት ደረጃ በመቀነስ ወይም በማጓደል የሚለቀቅ ፍሳሽ፣ | • ለግለሰብ ብር ፶ሺ.ህ<br>•ለድርጅት ብር ፻ሺ.ህ |
| | ለ) በራሱ ወይም ከሌላ ንጥረ ነገር ጋር በማዋሀድ መርዛማ ኬሚካል በማመንጨት በወንዙ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ፍሳሽ፣ | ብር ፬፻ሺ.ህ |

| | | |
|---|---|---|
| 3 | Discharges waste from a residential toilet or any untreated sewage into a river or pollutes a river by connecting the line; | • 150,000.00 Birr per individual<br>• 300,000.00 Birr for organization |
| 4 | Discharge treated sewage into a river without the consent of any person; | • 15,000.00 Birr per person<br>• 40,000.00 Birr for organization |
| 5 | When a permit is issued to discharge sewage into a river and it is controlled, the effluent does not meet the quality standards and has prohibited contents: | |
| | a) Sewage that is discharged from the sewage treatment plant and discharged into the river by reducing or degrading the quality level; | • 50,000.00 Birr for an individual<br>• 100,000.00 Birr for organization. |
| | b) Sewage that harms the river by generating toxic chemicals by itself or by mixing with other substances; | 400,000.00 Birr |

| | | |
|---|---|---|
| | ሐ) የፍሳሹ ፒኤች ከ6.0 ያነሰ ወይም ከ9.0 የሚበልጥ፣ | ብር ፻ሺ ህ |
| | መ) ከ100 ዲግሪ ሴንቲግሬድ በታች በሆነ ሙቀት ሊተኑ የሚችሉ ነገሮችን በውስጡ የያዘ ፍሳሽ፣ | ብር ፻ሺ ህ |
| | ሠ) በወንዙ ውሃ ላይ የሚፈነዳ ወይም መርዛማና አደገኛ ጋዝ ወይም ትነት የሚያመነጭ ፍሳሽ፣ | ብር ፬፻ሺ ህ |
| | ረ) ዘይት፣ ጨዋማ ፈሳሽ፣ የተቀጣጠለ የሞተር ዘይት፣ ነዳጅ ወይም ሳሙና ነክ የሆኑ እና ሌሎች የወንዙን ውሃ ተፈጥሮዊ ይዘት ሊቀይሩ የሚችሉ ነገሮች የያዘ ፍሳሽ፣ | ብር ፬፻ሺ ህ |
| | ሰ) አትክልትና ፍራፍሬ ተረፈ ምርቶችን፣ እንጨት፣ ጠጠር፣ አሸዋ፣ ጨርቅ፣ ድንጋይ የመሳሰሉትን በውስጡ የያዘ ፍሳሽ፤ | • ለግለሰብ ብር ፳ሺ ህ<br>• ለድርጅት ብር ፻ሺ ህ |



| | | |
|---|---|---|
| | c) PH of effluent less than 6.0 or greater than 9.0; | 100,000.00 Birr |
| | d) Effluent containing substances that can evaporate at temperatures below 100 degree Celsius; | 100,000.00Birr |
| | e) Leakage that explodes on the river water or produces poisonous and dangerous gas or vapor; | 400,000.00 Birr |
| | f) Drainagecontaining oil, salty liquid, burning motor oil, petrol or soapy substances and other substances that may change the natural composition of the river water; | 400,000.00 Birr |
| | g) Sewage containing vegetable and fruit by-products, wood, gravel, sand, cloth, stone, etc.; | • 20,000.00 Birr for an individual<br>• 100,000.00 Birr for organization |

| | | |
|---|---|---|
| ፮ | ማንኛውም በካይ ፍሳሽ ከተፈቀደው የፍሳሽ ማጠራቀሚያ ወይም የፍሳሽ መስመሩን ወደ ወንዝ ወይም የፍሳሽ መስመሩን ከጎርፍ መውረጃ ቦይ ጋር በማገናኘት ወደ ወንዝና ወንዝ ዳርቻ እንዲፈስ ማድረግ፤ | • ለግለሰብ ብር ፶ሺህ<br>• ለድርጅት ብር ፬፻ሺህ |
| ፯ | ኬሚካል ነክ ፍሳሾችን ተገቢውን የማከሚያ ዘዴ ሳይጠቀሙና ባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ያለው አካል ሳያረጋግጥ ወደ ወንዝና ወንዝ ዳርቻ መድፋት ወይም መልቀቅ፤ | • ለግለሰብ ብር ፶ሺህ<br>• ለድርጅት ብር ፫፻ሺህ |
| ፰ | ከአምራችና አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ማንኛውንም ያልታከመ ፍሳሽ ቆሻሻ ወደ ወንዝ በመልቀቅ ወይም መስመሩን ማገናኘት መበከል፤ | ብር ፫፻ሺህ |
| ፱ | የሽንት ቤት ፍሳሽ የማስወገድ ፈቃድ ወስዶም ሆነ ፈቃድ ሳይወስድ የሚሰራ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት በሚያስወግድበት ጊዜ ቀጥታ ወደ ወንዝ በመድፋት ወይም መቀላቀል፤ | ብር ፻ሺህ |

| | | |
|---|---|---|
| 6 | Any pollutant discharge from an approved septic tank or sewer line to a river or by connecting the sewer line to a flood drain to flow to a river or riverbank; | • 50,000.00 Birr for individual<br>• 400,000.00 Birr for organization |
| 7 | Throwing or releasing chemical spills into rivers and riverbanks without using appropriate treatment methods and without being verified by the authority or appropriate body; | • 50,000.00Birr for individual<br>• 300,000.00 Birr for organization |
| 8 | Contamination by releasing any untreated sewage from manufacturing and service-providing facilities into a river or connecting the line; | 300,000.00 Birr |
| 9 | Any individual or organization operating with or without a permit to dispose of toilet waste discharges it directly into the river or mixes it; | 100,000.00 Birr |

| | | |
|---|---|---|
| ፲ | በባህሪው አደገኛነት ያለው ደረቅም ሆነ ፍሳሽ ቆሻሻ ወደ ወንዝ መጣል ወይም እንዲጣል በማድረግ መበከል፤ | ለግለሰብ ብር ፭፻ሺህ ለድርጅት ብር ፩ ሚሊዮን |
| ፲፩ | በወንዝና በወንዝ ዳርቻ ክልል ውስጥ መጸዳዳት፤ | ብር ፪ሺህ |
| ፲፪ | የፍሳሽ ማጣሪያ ሳይኖረው በወንዝ ዳርቻ እና አካባቢ ላይ የተሽከርካሪ እጥበት ማከናወን፤ | ብር ፬፻ሺህ |
| ፲፫ | በወንዝ ዳርቻ ክልል ውስጥ እንስሳት ማሰማራት ወይም እንዲገቡ ማድረግ ወይም ከተፈቀደ መግቢያና መውጫ ውጭ ተሽከርካሪ ማሽከርከር፤ | ብር ፴፻ሺህ |
| ፲፬ | በወንዝና በወንዝ ዳርቻ ውስጥ ከተፈቀደው የመዝናኛ፣ መናፈሻና፣ ፓርክ እና ሌሎች ለወንዝ ዳርቻው ልማት አስፈላጊ ከሆነ ግንባታ ውጭ የፕላስቲክ ቤት ወይም ማንኛውም ዓይነት ግንባታ መገንባት፡፡ | ብር ፪፻ሺህ |

| | | |
|---|---|---|
| 10 | Disposing of hazardous solid or sewage waste into a river or polluting it by dumping; | • 500,000.00 Bir r for individual<br>• 1,000,000.00 B irr for organization |
| 11 | defecating in rivers and riverbank areas; | 2,000.00 Birr |
| 12 | Carrying out vehicle washing in and around riverbanks without sewage treatment; | 400,000.00 Birr |
| 13 | Grazing or allowing animals to enter the riverbank area or driving a vehicle outside the authorized entrance and exit; | 30,000.00 Birr |
| 14 | Constructing a plastic house or any type of construction outside of the permitted recreation, park, amusement park and other construction necessary for the development of the riverbank in the river and river banks. | 200,000.00 Birr |